አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሰላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፹
አዲስ አበባ መጋቢት ፯ ቀን ፳፻፲፭ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31st year No. 80
Addis Ababa, March 16th , 2023


**ማውጫ**


**አዋጅ ቁጥር ፹/፳፻፲፭**

**የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ጽህፈት ቤትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ**

ገጽ-------------------------------------፳፻፫


**CONTENTS**


**PROCLAMATION NO. 80/2023**

**SECRETARIAT OF THE ADDIS ABABA CITY COUNCIL RE-ESTABLISHMENT PROCLAMATION**

**Page ------------------------------------------2003**


## አዋጅ ቁጥር ፹/፳፻፲፭

## የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ጽህፈት ቤትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በቻርተር አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በሚገባ እንዲወጣ ለማስቻል እና ለምክር ቤቱ ሙያዊ ድጋፍና አስተዳደራዊ አገልግሎቶችን ማቅረብ የሚችል የራሱ የሆነ ጽህፈት ቤት ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፤

በሥራ ላይ የነበረው የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ምክር ቤቱ በአደረጃጀትና በአሰራር ላይ ያጋጠሙትን ችግሮች ለመቅረፍ እና ምክር ቤቱ ከደረሰበት የእድገት ደረጃ በሚመጥን መልኩ መሻሻል ያለበት በመሆኑ፤

## PROCLAMATION No. 80/2023
## A PROCLAMATION TO RE-ESTABLISH THE SECRETARIAT OF THE ADDIS ABABA CITY COUNCIL

WHEREAS, it is found necessary to enable the City Council of Addis Ababa to perform the duties and responsibilities enshrined under the Revised Charter of the City;

WHEREAS, it has become necessary to amend the existing establishment proclamation of the Secretariat of the Addis Ababa City Council to be compatible with the level of development of the Council and to solve the problems faced by the office in terms of organization and operation;


ያንዱ ዋጋ..........
Unit price..........

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ ዓ.ም አንቀፅ ፲፬ ንዑስ አንቀፅ (፪) ተራ ፊደል (ሠ) መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር ፹/፪ሺ፲፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

፩. **"አዋጅ"** ማለት የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ ነው፣

፪. **"ምክር ቤት"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ነው፤

፫. **"አፈ ጉባዔ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ነው፤

፬. **"ጽህፈት ቤት"** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ጽህፈት ነው፤

፭. **"ጽህፈት ቤት ኃላፊ"** ማለት በዚሁ አዋጅ መሰረት የተቋቋመውን የምክር ቤት ጽህፈት ቤት እንዲመራ በአፈ-ጉባኤው የሚሾም ሰው ነው::

**፫. የፆታ አገላለፅ**

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ያጠቃልላል፡፡

NOW, THEREFORE, in accordance with sub Article 2(e) of Article 14 of the Revised Charter Proclamation No 361/2003 of Addis Ababa the City Council has issued this Proclamation as follows:

## Part one

## General Provisions

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Secretariat of the Addis Ababa City Council Re-establishment Proclamation No. 80/2023."

**2. Definitions**

In this Proclamation unless the context otherwise requires:

1. **"Proclamation"** means the revised Addis Ababa City Administration Charter proclamation No. 361/2003.
2. **"Council"** means Addis Ababa City Council;
3. **"Speaker"** means Speaker of the City Council Addis Ababa ;
4. **"Secretariat"** means the Secretariat of the Addis Ababa City Council established pursuant Article 3 of the Proclamation;
5. **"Head of the Secretariat"** means the person appointed by the speaker to head the Secretariat of the Council established in accordance with this Proclamation.

**3. Gender**

Any expression in the masculine gender includes the feminine.

## ክፍል ሁለት

## መቋቋም፣ አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር

**፬. መቋቋም**

፩. የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ከዚህ በኋላ “ጽህፈት ቤት” እየተባለ የሚጠራ ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል፤

፪. የጽህፈት ቤቱ ተጠሪነት ለአፈ-ጉባኤ ይሆናል፡፡

**፭. ዓላማ**

ጽህፈት ቤቱ የተቋቋመበት ዓላማ ምክር ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ለማሳካት የሚያስፈልጉ ሙያዊ ድጋፍና አስተዳደራዊ አገልግሎቶችን ለመስጠት ነው፡፡

**፮. የጽህፈት ቤቱ አደረጃጀት**

፩. ጽህፈት ቤቱ የሚከተለው አደረጃጀት ይኖረዋል፡-

ሀ) ዕውቀትና ችሎታ ያለው ገለልተኛና ባለሙያ የሆነ በአፈ-ጉባኤው የሚሾም የጽህፈት ቤት ኃላፊ፤

ለ) ሌሎች ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ የሥራ ክፍሎች እና ሠራተኞች፤

፪. በዚህ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከቱት የጽህፈት ቤቱ አካላት ደመወዝ፣ ጥቅማጥቅም እና አበል የአስተዳደሩን የፋይናንስ አቅም ያገናዘበ እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር በምክር ቤቱ አማካሪ ኮሚቴ ይወሰናል፡፡

## Part Two

## Establishment, Organizational Structure Powers and Function

**4. Establishment**

1. The Secretariat of the City Council of Addis Ababa (hereinafter called the “Secretariat) hereby re- established as an organ having legal personality;
2. The Secretariat shall be accountable to the speaker.

**5. Objective**

The objective for which the Secretariat is established shall be to provide professional support and administrative services to the Council in order to enable it effectuate to achieve its powers and functions.

**6. Organization of the Secretariat**

1. The Secretariat shall have:
   A) A head of secretariat to be appointed by the Speaker who is a neutral, professional and competent;
   B) The necessary staff and departments.

2. The salaries, benefits and allowances of the members of the office referred to in this subsection (1) shall be decided by the advisory committee of the Council, taking into account the financial capacity of the administration and consulting with the relevant parties.

**፯. <u>የጽሕፈት ቤቱ ሥልጣንና ተግባራት</u>**

ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. ለምክር ቤቱ ህግ አወጣጥ፣ ክትትል ቁጥጥር እና ለሕዝብ ውክልና ሥራዎች የሚያስፈልጉ ሙያዊ ድጋፍና አስተዳደራዊ አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

፪. በምክር ቤቱ ለሚቋቋም ኮሚቴና ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች አጠቃላይ አስተዳደራዊ አገልግሎትና ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤

፫. ምክር ቤቱ ያፀደቀውን ሕግ በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ያሳትማል፣ ያሰራጫል፤ ያስተዳድራል፤

፬. የምክር ቤቱን ረቂቅ በጀት አዘጋጅቶ ለአፈ-ጉባኤ ያቀርባል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፭. ለምክር ቤቱ አባላት በህግ የተወሰኑ ጥቅማ ጥቅሞች እና ልዩ መብቶችን ያስፈጽማል፤

፮. ለምክር ቤቱና ለምክር ቤቱ የተለያዩ አካላት የቃለ-ጉባዔ፣ የአዳራሽ አገልግሎት፣ የህትመትና ሌሎች የኮንፈረንስ አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

፯. የምክር ቤቱን ቃለ ጉባዔ እና ውሣኔ ቁጥር እየተሰጠው በሚገባ ተመዝግበው እንዲጠበቁ ያደርጋል፤

፰. ለምክር ቤቱ አባላትና ተገልጋዮች የቤተ-መጻሕፍት፣ የምርምር፣ የመረጃና ዶክመንቴሽን አገልግሎት ይሰጣል፤

፱. ለምክር ቤቱ አባላትና እንግዶች አስፈላጊውን የመስተንግዶ አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፤

**7. <u>Powers and Duties of the Secretariat</u>**

The Secretariat shall have the powers and duties to:

1. provide professional support and administrative services necessary for the effectiveness of the legislative, supervision and oversight, and representation mandate of the Council;
2. Provides general administrative services and professional support to committees and various organizations established by the council;
3. the Council will publish, distribute and administer the law adopted by the Addis Negari Gazeta;
4. prepares the draft budget of the Council and submits it to the speaker; It will be implemented when approved by the concerned body;
5. enforce the benefits and special privileges determined by law to members of the Council;
6. provides meeting minutes, hall service, publication and other conference services to the Council and its various bodies;
7. ensures that the minutes and resolutions of the Council are properly recorded and kept properly;
8. provides library, research, information and documentation services to the members and users of the Council;
9. Provides the necessary cordiality services for the members and guests of the council;

፲. የንብረት ባለቤት ይሆናል፤ ንብረቱንም ያስተዳድራል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፲፩. ለጽህፈት ቤቱ ሠራተኞች የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ይሰራል፤

፲፪.ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ የሕዝብ ግንኙነት፣ የገጽታ ግንባታ እና ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፰. <u>የምክር ቤት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር</u>

የጽህፈት ቤት ኃላፊው ተጠሪነት ለአፈ-ጉባዔው ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

፩. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ የተመለከቱትን የጽህፈት ቤቱን ሥልጣንና ተግባር ሥራ ላይ ያውላል፤

፪. የጽሕፈት ቤቱን የሠራተኞች አስተዳደር፣ እድገት፣ ቅጥርና ስንብት አፈፃጸም በአስተዳደሩ የመንግስት ሠራተኞች ህግ መሰረት በማከናወን ለአፈ-ጉባዔው አቅርቦ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፫. የጽሕፈት ቤቱን ዓመታዊ በጀትና የሥራ ዕቅድ በማዘጋጀት ለአፈ-ጉባኤ ያቀርባል፤ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፬. በተፈቀደው በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ በማድረግ ሥራ ላይ ያውላል፤

፭. የጽሕፈት ቤቱን የሥራ እቅድ አፈፃፀምና የሂሣብ ሪፖርት በማዘጋጀት ለአፈ-ጉባኤ ያቀርባል፤

፮. የጽሕፈት ቤቱን ንብረት በከተማ አስተዳደሩ የንብረት አስተዳደር ህግ መሰረት ያስተዳድራል፤

10. Own property, administer his property, enter into contract, sue and be sued in its own name;
11. undertake capacity building activities for secretariat staff;
12. perform public relations and such other activities that are necessary to the attainment of its objectives.

## 8. <u>Power and Function of Head of the Secretariat</u>

The head of the Secretariat is accountable to the Speaker and has the following powers and duties:-

1. exercise the powers and duties of the Secretariat provided under Article 7 of this Proclamation;
2. employ and administer, promotion, and dismissal of employees engaged in support services of the Secretariat in accordance with the administration's law on government employees, and will be submitted to the Speaker and implemented upon approval;
3. prepare annual budget and work program of the Secretariat and implement same upon approval;
4. Effect expenditure in accordance with approved budget of the Secretariat;
5. prepare and submit to the Speaker the performance and financial reports of the Secretariat;
6. Administer property of the Secretariat in accordance with property administration law of the City;

፯. ጽህፈት ቤቱ ከሶስተኛ ወገን ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ጽህፈት ቤቱን ይወክላል፤

፰. ጽህፈት ቤት ኃላፊው ለጽህፈት ቤቱ የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለጽህፈት ቤቱ ሌሎች የሥራ ክፍል ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

፱. በአፈ ጉባኤ የሚሰጡትን ሌሎች ተጨማሪ ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ክፍል ሶስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፱. በጀት
የጽሕፈት ቤቱ በጀት በከተማው ምክር ቤት ይመደባል፡፡

### ፲. የሂሣብ መዛግብት

፩. ጽሕፈት ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፤

፪. የጽሕፈት ቤቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በከተማው ዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ፤

፫. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤ በማናቸውም አስፈላጊ ጊዜና ሰዓት የሂሣብ መዛግብትና የሂሳብ ሰነዶችን በዋናው ኦዲተር እንዲመረመሩ ሊያደርግ ይችላል፡፡

7. Represent the Secretariat in its dealings with third parties.
8. The head of the Secretariat may delegate part of his power and duties to other officials and employees of the secretariat to the extent necessary for the efficient performance of the Secretariat;
9. Performs other additional duties assigned by the Speaker.

## Part Three
## Miscellaneous Provisions

### 9. Budget
The budget of the Secretariat shall be allocated by the Council.

### 10. Books of Accounts
1. The Secretariat shall keep accurate and complete books of accounts.
2. The books of accounts and financial documents of the Secretariat shall be audited annually by the City Auditor General or an auditor designated by him;
3. without prejudice sub article (2) of this Article, the Speaker of the Council may, at any necessary time and place, have the accounts and accounting documents examined by the Auditor General .

**፲፩. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

፩. ምክር ቤቱ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፤

፪. አፈ ጉባኤው ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፪. የተሻሩ ህጎች**

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፬/፪ሺ.፬ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

**፲፫. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከ መጋቢት ፯ ቀን ፪ሺ.፲፭ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፯ ቀን ፪ሺ.፲፭ ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**11. Power to Issue Regulation and Directive**

1. The Council may issue regulation for the implementation of this proclamation;
2. The Speaker may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation.

**12. Repealed Laws**

The Secretariat of the Addis Ababa City Council Establishment Proclamation No. 34/2012 is hereby repealed.

**13. Effective Date**

This Regulation shall enter into force as of this 16 th day of March 2023.

**Done at Addis Ababa, this 16th day of March, 2023.**

**ADANECH ABIEBIE**

**MAYOR OF ADDIS ABABA CITY**